# የወንጀል ምርመራ መዝገብን  የማቋረጥና የመዝጋት፣ የክስ መዝገብን የማቋረጥ አሠራር ሥርዐትን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2012

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 በመቋቋሙና ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለያየ ተቋም የነበረውን የወንጀል ምርመራ መዝገብ የማቋረጥና የመዝጋት እንዲሁም የክስ መዝገብ የማቋረጥና የማንቀሳቀስ አሰራር ከአዲሱ ተቋም ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የወንጀል ምርመራ መዝገብ የሚቋረጥበትና የሚዘጋበት እንዲሁም ክስ የሚቋረጥበት ሥርዓት ወጥ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ማስቻል በማስፈለጉ፤

የወንጀል ምርመራ መዝገብን የማቋረጥና የመዝጋት እንዲሁም ክስ የማቋረጥና የማንቀሳቀስ ሂደት ከብልሹ አሰራር የፀዳ ለማድረግ፣ እንዲሁም በቂ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ "በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008" አንቀጽ 21(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የምርመራ መዝገብን የማቋረጥና የመዝጋት እና የክስ መዝገብን የማቋረጥ የአሠራር ሥርዐት ለመዘርጋት የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. **"ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ"** ማለት በፌዴራል ጠቅላይ  ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
2. **"ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ"** ማለት የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ ነው፡፡
3. "**ዐቃቤ ሕግ**" ማለት እንደአስፈላጊነቱ የፌዴራል ጠቅላይ  ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

4. **“የምርመራ መዝገብ ማቋረጥ”** ማለት በፖሊስ ወይም በዐቃቤህግ በመመርመር ላይ ያለን መዝገብ ሂደቱ እንዳይቀጥል ማቋረጥ ማድረግ ነው፡፡
5. **“የምርመራ መዝገብ መዝጋት”** ማለት በዐቃቤህግ የሚሰጥ የአያስከስስም ውሳኔ ነው፡፡
6. **“የክስ መዝገብ”** ማለት ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ የመሰረተበት ማንኛውም መዝገብ ነው፡፡
7. **“ጽሕፈት ቤት”** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ምድብ ጽሕፈት ቤት ወይም በክልል የሚገኝ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡
8. **“ኃላፊ”** ማለት የምድብ ጽሕፈት ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ነው፡፡
9. **“ምክትል ኃላፊ”** ማለት የምድብ ጽሕፈት ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ ነው፡፡
10. **“ዳይሬክቶሬት ወይም ዳይሬክተር”** ማለት በክርክር ጉዳዮች ዘርፍ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤህግ የተደራጀና የወንጀል ምርመራና ክስ ላይ የሚሰራ ዳይሬክቶሬት ወይም ዳይሬክተር ነው፡፡
11. **“ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት”** ማለት የሕግ ጉዳዮች ኦዲትና ኢንስፔክሽን፣ ቅሬታ ማስተናገጃና ሥነ ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡
12. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የፌዴራል የወንጀል ምርመራ መዝገብን ምርመራ ማቋረጥ፣ መዝጋት እንዲሁም የክስ መዝገብን ማቋረጥ ውሳኔ በሚሰጥባቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>መርህ</u>

የወንጀል ምርመራ መዝገብን የማቋረጥና የመዝጋት እንዲሁም ክስ የማቋረጥ ውሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ እና ሕጉ በሚጠይቀው መልኩ በበቂ ትንታኔና በግልጽ የተቀመጠ ሆኖ በተጠያቂነት መርህ የሚመራ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የወንጀል ምርመራ መዝገብ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

## ንዑስ ክፍል አንድ

### የወንጀል ምርመራ መዝገብን ስለ ማቋረጥና ስለማንቀሳቀስ

5. **የወንጀል ምርመራ መዝገብን ስለ ማቋረጥ**
    1. የወንጀል ምርመራ መዝገብ ምርመራው የሚቋረጠው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ብቻ ነው፡፡
    2. ምርመራው እንዲቋረጥ የሚሰጠው ትዕዛዝ በጽሑፍ ሆኖ ምርመራው የሚቋረጥበትን ምክንያት በዝርዝር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡
6. **የተቋረጠ መዝገብን ስለማንቀሳቀስ**

1. የተቋረጠ የምርመራ መዝገብ እንደገና ሊንቀሳቀስ የሚችለው መዝገቡን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የቀረ ወይም የተለወጠ ከሆነ ነው፡፡

2. የተቋረጠ የምርመራ መዝገብ እንደገና ማንቀሳቀስ የሚችለው፡-

ሀ. ምርመራው የተቋረጠው በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ከሆነ በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤህጉ ወይም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ትእዛዝ፣

ለ. ምርመራው የተቋረጠው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትእዛዝ ከሆነ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ትእዛዝ፤

ብቻ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

### የወንጀል ምርመራ መዝገብን ስለ መዝጋት

7. <u>የወንጀል ምርመራ መዝገብ የሚዘጋበት ምክንያቶች</u>

የወንጀል ምርመራ መዝገብ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊዘጋ ይችላል፡፡

1. ጉዳዩ የወንጀል ባህሪ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. ተጠርጣሪው በሕይወት የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
3. የተጠርጣሪው ዕድሜ ከዘጠኝ ዓመት በታች መሆኑ ሲረጋገጥ፤
4. ተጠርጣሪው ያለመከሰስ መብት ያለው ከሆነና ይህ ልዩ መብቱ ያልተነሳ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
5. ተጠርጣሪውን ማግኘት የማይቻልና ክሱ በሌለበት ሊታይ የማይችል ከሆነ፤
6. ወንጀል ፈፃሚውን ማወቅ ያልተቻለ ከሆነ፤
7. ምርመራ በተደረገበት ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ተጠርጣሪው ከዚህ በፊት ተከሶ ነፃ ስለመውጣቱ ወይም ጥፋተኛ ስለመባሉ የተረጋገጠ ከሆነ ወይም ተጠርጣሪው በሌላ ቦታ ክስ ቀርቦበት በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ወይም በምርመራ ላይ ያለ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ፤
8. ምርመራ የተደረገበት ጉዳይ በይርጋ የታገደ ወይም በምህረት ቀሪ የተደረገ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
9. በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ላይ አመልካቹ ጉዳዩን ከተወው፣
10. ክስ መስርቶ ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ የሆነ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ፤ እንዲሁም
11. በሕግ በግልጽ በተመለከቱ ጉዳዮች፡፡

8. <u>የምርመራ መዝገብ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>

1. የምርመራ መዝገብ ላይ የመዝጋት ውሳኔ መስጠት የሚችለው ምርመራውን የመራው ዐቃቤ ሕግ ፣ እርሱን ተክቶ የመረመረው ወይም መዝገቡ የተመራለት ዐቃቤ ሕግ ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት፡-

   ሀ/ የምርመራ መዝገቡ ለውሳኔ ከመቅረቡ በፊት ምርመራው የተጠናቀቀ ስለመሆኑ፣

ለ/ ምርመራ መዝገቡን ለመዝጋት ምክንያት የሆነው ፍሬ ነገር ለማሟላት ተገቢና ምክንያታዊ ጥረት ስለመደረጉ፤

መረጋገጥ አለበት ።

## 9. የምርመራ መዝገብ የመዝጋት ውሳኔ ይዘት

ዐቃቤሕግ የወንጀል ምርመራ መዝገብ ላይ የመዝጋት ውሳኔ ሲወስን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔው የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

1. ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፣የፖሊስ ምርመራ መዝገብ ቁጥር፣ የዐቃቤ ሕግ መዝገብ ቁጥር፤
2. ምርመራውን ያከናወነው የፖሊስ ተቋም ስም፤
3. የተጠርጣሪውን ስም(ያልታወቀም ከሆነ ይህንኑ በመግለጽ)፤
4. የተጠረጠረበትን የወንጀል ዓይነት፤
5. የወንጀል ተጎጅውን /የአቤቱታ አቅራቢውን ስም/፤
6. ተፈፀመ በተባለው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰ ጉዳት፤
7. የተጠርጣሪው ቃል፤
8. የማስረጃዎች ዓይነትና ይዘት፤
9. ማስረጃዎችንና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት በማድረግ ዐቃቤ ሕግ የውሳኔውን ምክንያት በግልጽ በመተንተን የሰጠውን ውሳኔ፤
10. ውሳኔውን የሰጠው ዐቃቤ ሕግ ስምና ፊርማ፤
11. ውሳኔውን የሰጠው ጽሕፈት ቤት ወይም ዳይሬክቶሬት ማሕተም፤
12. ኤግዚቢት ላይ የተሰጠ ውሳኔ፤
13. የውሳኔ ግልባጭ የሚደረግላቸውን አካላት፡፡

## 10. ግልባጭ ስለማድረግ

የምርመራ መዝገብ ከተዘጋ በኂላ ውሳኔው፡-

1. ለግል ተበዳይ፤
2. ጽሕፈት ቤት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ የወንጀል ጉዳዩ ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት፤
3. ዳይሬክቶሬት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፤
4. ለኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት፤
5. ሌሎች ለሚመለከታቸው ፤

ግልባጭ መደረግ አለበት፡፡

## 11. የወንጀል ምርመራ መዝገብ ከተዘጋ በኋላ መከተል ስለሚገባው ሥነሥርዐት

1. ውሳኔው የተሰጠው በጽሕፈት ቤት ባለ ዐቃቤ ሕግ ከሆነ ውሳኔው ከመላኩ በፊት ውሳኔው ሕጉን የተከተለ ስለመሆኑ በኃላፊው ወይም በምክትል ኃላፊው ይረጋገጣል፡፡
2. ውሳኔው የተሰጠው በዳይሬክቶሬት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ ከሆነ የውሳኔ ግልባጩ ከመላኩ በፊት ውሳኔው ሕጉን የተከተለ ስለመሆኑ በአስተባባሪው ወይም በዳይሬክተሩ ይረጋገጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት በውሳኔው ካልተስማማ መዝገቡን ለቡድን ውይይት ይመራዋል፤ የውይይቱን ቃለ ጉባዔ መዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ያደርጋል፤ ሆኖም ዐቃቤሕጉ የሰጠው ውሳኔ አይለወጥም፡፡
4. የውሳኔው ዋና ቅጂ ምርመራውን ላከናወነው የፖሊስ ተቋም ይላካል፡፡
5. የግል ተበዳዩ ውሳኔው እንዲሰጠው በአካል ቀርቦ የጠየቀ እንደሆነ የውሳኔ ግልባጭ ይሰጠዋል፡፡
6. በዚህ ሕግ አንቀጽ 10 ላይ ለተዘረዘሩት የውሳኔው ግልባጭ ይላካል፡፡

## 12. በተዘጋ መዝገብ ላይ የዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

በተዘጉ መዛግብት ላይ ዳይሬክቶሬቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

1. ከጽሕፈት ቤት ግልባጭ የተደረገለትን እንዲሁም በዳይሬክቶሬቱ የምርመራ መዝገብ ላይ የተሰጠን ውሳኔ አደራጅቶ የመያዝ፤

2. ከጽሕፈት ቤት ግልባጭ የተደረገለትን ውሳኔ ሕግን ተከትሎ የተሰጠ ውሳኔ መሆኑን የማረጋገጥ፤
3. የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የለውም ብሎ ካመነ የወንጀል ምርመራ መዝገቡን አስቀርቦ የመመርመር፣ ትንታኔ ወይም ማብራሪያ መጠየቅ፣ እንዲሁም የተዘጋው መዝገብ ላይ ተጨማሪ ምርመራ ማካሄድ ወይም ክስ መመስረት ይገባል ብሎ ካመነ ሀሳቡን ለኦዲትና ኢንስፔክሽን በጽሑፍ ማሳወቅ፤
4. የተዘጉ መዝገቦች ላይ መስተካከል ያለባቸውን ችግሮች በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ የማመላከት፣ ለበላይ አመራሩ ሪፖርት የማቅረብ፤
5. በሪፖርት ወይም በአቤቱታ የተገኙ ድክመቶች እንዲስተካከሉ ማድረግ፤
6. ከጽሕፈት ቤት በመጣ መዝገብ ላይ በግል ተጠያቂ መሆን ያለበት ዐቃቤ ሕግ ካለ ሀሳቡን ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ማሳወቅ፤
7. በዳሬክቶሬቱ መዝገብ ላይ ተጠያቂ መሆን ያለበት ዐቃቤ ሕግ ካለ ለዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የማቅረብ፡፡

13. <u>በተዘጋ መዝገብ ላይ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በተዘጉ መዝገቦች ላይ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ከጽሕፈት ቤቶችና ከዳይሬክቶሬቶች ግልባጭ የተደረጉለትን ውሳኔዎች አደራጅቶ መያዝ፤
2. የተዘጉ መዝገቦች በሙሉ ግልባጭ የተደረጉለት መሆኑን ማረጋገጫ መጠየቅ፤ በአካልና በማንኛውም መንገድ ማጣራት፤
3. የሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን በሚካሄድበት ጊዜ የተገኙ ድክመቶች እንዲስተካከሉ፤ በግል ተጠያቂ መሆን ያለባቸውን አግባብ ባለው መንገድ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ፤
4. የተሰጠው ውሳኔ አሳማኝ ባልሆነ ጊዜ መዝገቡን አስመጥቶ የመመርመር፤ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግበት ወይም ክስ እንዲመሰረት ውሳኔውን በጽሑፍ በመግለጽ ለጽሕፈት ቤቱ ወይም ለዳይሬክቶሬቱ መመለስ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የክስ መዝገብ ስለማቋረጥ እና ስለማንቀሳቀስ

### 14. የክስ መዝገብ ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች

1. ማንኛውም የክስ መዝገብ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ሊቋረጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ክስ የሚቋረጠው፡-

   ሀ/ የተከሳሽ ማንነት ላይ ስህተት ሲያጋጥም፤

   ለ/ የሕዝብ ጥቅምን ለማስከበር ሲባል፤ ወይም

   ሐ/ በሌሎች ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡፡

### 15. የክስ መዝገብ ስለማቋረጥ

1. በክስ መዝገቡ ላይ ያለው ተከሳሽ በስህተት ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ የጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ፣ ዳይሬክተር፣ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ክስ የማቋረጥ ትእዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
2. የቀረበው ክስ የሕዝብ ጥቅምን የማያስከብር መሆኑ ሲታመንበት ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲቋረጥ ትእዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም በሙስና እን በገቢዎችና ጉምሩክ ወንጀል ጉዳዮች ላይ የተመሰረቱ ክሶች የሚነሱት በጠቅላይ ዐቃቤሕጉ ብቻ ነው፡፡
4. በሌላ ማናቸውም ጉዳይ ክሱ ሊቋረጥ የሚችለው በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ትእዛዝ ብቻ ነው፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ምክንያት ክሱ ሊቋረጥ ይገባል ብሎ የሚያምን ኃላፊ ወይም ዳይሬክተር ሀሳቡን በዝርዝር ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በጽሑፍ በማቅረብ እንዲወሰን ማድረግ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የተዘረዘሩት ቢኖሩም በችሎት ላይ ያለ ዐቃቤ ሕግ ክሱ ሊቋረጥ ይገባል ብሎ የሚያምንበት ምክንያት ሲፈጠር በስነ ስርዓት ሕጉ መሰረት ተገቢውን ቀጠሮ በመጠየቅ ከኃላፊው ወይም ከዳይሬክተሩ ጋር በመነጋገር ኃላፊው ወይም ዳይሬክተሩ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

16. <u>የክስ መዝገብ የሚቋረጥበት አሰራር ሂደት</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 መሰረት የክስ ማቋረጥ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ በጽሑፍ ሆኖ በበቂ ትንታኔ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡
2. ክሱ የተቋረጠው በጽሕፈት ቤት ከሆነ ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በዳይሬክቶሬት የተቋረጠ ከሆነ ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በግልባጭ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. ክሱ የተቋረጠው በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤህግ ከሆነ ለጠቅላይ ዐቃቤህግ በግልባጭ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የክስ መዝገብ የማቋረጥ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ለኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ግልባጭ መደረግ አለበት፡፡

17. <u>የተቋረጠ የክስ መዝገብን ስለማንቀሳቀስ</u>

የተቋረጠ የክስ መዝገብ እንደገና ሊንቀሳቀስ የሚችለው፡-

1. ያቋረጠው አካል በሚሰጠው ዝርዝር ትንታኔን በያዘ ትእዛዝ፤
2. ክሱ የተቋረጠበት ምክንያት በየደረጃው ባለ ኃላፊ ተመርምሮ ትክክል አለመሆኑ ሲረጋገጥ፤ ወይም
3. የተቋረጠበት ምክንያት ጊዜያዊ ሆኖ መዝገቡን ለማቋረጥ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ሲኖርና መሟላቱ ሲረጋገጥ፤

ነው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለ አቤቱታ</u>

18. <u>በመዝገብ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ በጠቅላላ</u>

1. ማንኛውም በምርመራ መዝገብ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ቅሬታ ዐቃቤ ህጉ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ ሊቀርብ አይገባውም፤ ሆኖም የክስ መዝገብ መቋረጥን በሚመለከት በማንኛውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም የህዝብ ጥቅምን በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታ ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በማንኛውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**19. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

በምርመራ መዝገብ መዘጋት ወይም መቋረጥ ላይ፡-

1. የወንጀል ተጎጂ/የግል ተበዳይ/ ወይም ሕጋዊ ወኪል፣
2. የወንጀል ተጎጂ ቤተሰብ፣
3. ፖሊስ፣
4. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው የተነካ ሰዎች፣
5. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም ሰዎች፣

ቅሬታዎችን ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**20. <u>የምርመራ መዝገብ መዘጋት አቤቱታን ስለመስማት</u>**

በተዘጋ የምርመራ መዝገብ ላይ እንደቅደም ተከተላቸው፡-

1. በጽሕፈት ቤት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ በተሰጠ ውሳኔ ላይ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፣ ዳይሬክተር፣ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፤
2. በዳይሬክቶሬት ስር ባለ ዐቃቤ ሕግ በተሰጠ ውሳኔ ላይ የዳይሬክቶሬቱ አስተባባሪ፣ ዳይሬክተር፣ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፤

ቅሬታን ይቀበላሉ፡፡

**21. <u>የምርመራ መዝገብ መቋረጥ አቤቱታን ስለመስማት</u>**

1. የምርመራ መዝገብ መቋረጥ የተመለከተ ቅሬታ ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የሚቀርብ ሲሆን በውሳኔው ላይ ያለ ቅሬታ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ይቀርባል፤ የጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡
2. አቤቱታው በአንቀጽ 22(3) እና (4) መሰረት ይመረመራል፡፡

**22. <u>አቤቱታ ስለሚመረመርበት አግባብ</u>**

1. ለጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሚቀርብ ቅሬታ በኃላፊው የሚወሰን ሆኖ ውሳኔውን ከሰጠው ዐቃቤ ሕግ ጋር በመነጋገር እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱና እንደመዝገቡ ሁኔታ የዐቃቤያነ ሕግ ቡድን በማቋቋም እንዲመረመር ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ለዳይሬክቶሬት የሚቀርብ ቅሬታ፡-

ሀ/ ለዳይሬክቶሬቱ አስተባባሪ የሚቀርብ ቅሬታ ውሳኔውን ከሰጠው ዐቃቤ ሕግ ጋር በመነጋገር በአስተባባሪው ይወሰናል፡፡

ለ/ ለዳይሬክተሩ የሚቀርብ ቅሬታ በዳይሬክተሩ የሚወሰን ሆኖ የዐቃቢያነ ሕግ ቡድን በማቋቋም የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡለት ያደርጋል፡፡ ቡድኑ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና መዛግብትን ደብዳቤ በመጻፍ በዳይሬክተሩ ፊርማ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡

3. ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚቀርብ አቤቱታ በምክትሉ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሚቋቋም ቡድን ተመርምሮ ውሳኔው በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ወጭ ይደረጋል፡፡

4. ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የሚቀርብ ቅሬታ፡-

ሀ/ በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ፣ በአማካሪዎቻቸው፣ ወይም በጊዜያዊነት በተቋቋመ ቡድን ተመርምሮ በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ፊርማ ወጭ ይደረጋል፡፡

ለ/ የጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡

## 23. አቤቱታ የሚሰማ አካል ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ መሠረት ቅሬታን እንዲያስተናግድ የተገለጸ አካል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. የሚቀርብላቸውን ቅሬታ መዝግቦ የመያዝ፤
2. የቀረበውን ቅሬታ ቀላል ወንጀል ከሆነ በ10 ቀን፣ ለመካከለኛ ወንጀል በ15 ቀን እንዲሁም ለከባድ ወንጀል በ20 ቀን ውስጥ መልስ መስጠት፤
3. ለቀረበው ቅሬታ በጽሑፍ መልስ መስጠት፤
4. የቀረበውን ቅሬታ ያልተቀበሉት ከሆነ ያልተቀበሉበትን ምክንያት ለባለጉዳዩ የማስረዳትና በጽሑፍ መልስ በመስጠት ባለጉዳዩ በተሰጠው ዉሳኔ ላይ ካልተስማማ በቀጣይ አቤቱታውን ማቅረብ የሚችልበትን አካል የመግለጽ ግዴታ አለባቸው፡፡
5. ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም ሲባል "ቀላል ወንጀል" ማለት እስከ ሦስት ዓመት ቀላል እስራት፣ "መካከለኛ ወንጀል" ማለት እስከ አስራ አምስት ዓመት እስራት፣ እንዲሁም "ከባድወንጀል" ማለት ከአስራ አምስት ዓመት በላይ እስራት ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ነው ፡፡

24. <u>የክስ መዝገብን መቋረጥ በተመለከተ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>

በዚህ ክፍል ስለ አቤቱታ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ለክስ መቋረጥ እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

25. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች</u>

1. በወንጀል ፍትህ አስተዳደር የወንጀል ምርመራን ማቋረጥ፣ የምርመራ መዛግብትን መዝጋት እና ክስ መቋረጥ በሚመለከት በመጋቢት 12/2006 ዓ.ም በፍትሕ ሚኒስቴር የወጣው የአሰራር ስርዓት መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

26. <u>የሥነ ምግባር ተጠያቂነት</u>

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መተላለፍ ወይም በመመሪያው መሠረት ተግባራትን አለማከናወን በዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ደንብ መሰረት የዲስፕሊን ቅጣት ያስከትላል፡፡

27. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በ 1 ወር ጊዜ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ….. ቀን 2009 ዓ.ም**

**አቶ ጌታቸው አምባዬ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ**